# በግንቦት 7 ውስጥ የተጀመረው ትርምስ አሁንም እንደቀጠለ ነው!

## የእርምት ንቅናቄ ቡድኑ ለአመራሩና ለአባላት ማስጠንቀቂያ-አዘል የውስጥ ማስታወሻ በትኗል!!

የግንቦት 7 የእርምት ንቅናቄ ብሎ ራሱን የሚጠራው ቡድን በተደጋጋሚ ላቀረባቸው ጥያቄዎች አመራሩ "ጆሮ ዳባ ልበስ" በማለት በጀመረው የአምባገነንት እና የፈላጭ ቆራጭነት መንገዱ ከቀጠለ በድርጅቱ፣ በትግሉና በአባሉ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂው አመራሩና አመራሩ ብቻ እንደሚሆን በማስጠንቀቅ ለአባላት የበተነው የውስጥ ማስታወሻ አሁንም የድርጅቱ አመራርና አባላትን እያተራመሰ ይገኛል፡፡

ከዚህ ቀደም በድርጅቱ ውስጥ ለአባላት የተበተኑ እስከአሁን ድረስ በእጄ ያልገቡ ፅሑፎች መኖራቸውንም ተረድቻለሁ፡፡

የግንቦት 7 የእርምት ንቅናቄ ብሎ ራሱን ከሚጠራው ከዚህ ቡድን ውጪ ሌሎች ቡድኖችም እየተፈጠሩ መምጣታቸውን የሚያሳዩ ምልክቶች አሉ፡፡

የግንቦት 7 የእርምት ንቅናቄ ቡድን በማለት ራሱን የሚጠራው ይኸው ቡድን

"የግንቦት 7 መሪዎቻችን በውስጥ ተቃዋሚነት የሚጠረጠሩ አባላትን በተናጠል የማባባልና የመምታት ከንቱ እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው!

የዲያስፖራው ገንዘብም ሆነ ድጋፍ አያስፈልገንም እያሉንም ነው!!"

በሚል ርዕስ ለአባላት የበተነው ባለ 3 ገፅ ማስጠንቀቂያ-አዘል ማስታወሻ ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ ልኬላችኋለሁ፡፡ ቀደም ሲል በገባሁላችሁ ቃል መሰረት ሌሎች ፅሑፎችም ሲደረሱኝ እልከላችኋለሁ፡፡

ወዳጃችሁ

ከስዊዘርላንድ